# ሶስት አይነት እምነቶች

እኛ የምናውቀው ፤ ሰንደቅ አላማችን
ሕብረ ብሄራዊ ፣ ያለው በደማችን
አረንጓዴ ቢጫ ፣ ቀይ ነው አርማችን
የማማ ኢትዮጵያ ፣ እናት ሐገራችን ።

እርግጥ ነው ነበረ ፣ ምስል ከመሃሉ
ዘውድ የደፋ አንበሳ ፣ እስከነ መስቀሉ
ደርግ የሚባል አውሬ ፣ አረም የበቀሉ
አንበሳና ዘውዱን ፣ በድፍረት ሳይከሉ ።

መስቀል የክርስቲያን ፣ ዘውድም የንጉሥ ነው
ብሎ ሲያወናብድ ፣ ሲኮንን ሲከሰው
በማጭድ መዶሻ ፣ ተክቶ ሲያፈርሰው
የክህደት መንገዱን ፣ መች አስተዋለው ሰው ።

ህዝቡም በመገረም ፣ በመደነቅ ሳለ
እስላም ክርስቲያኑን ፣ ያዋህዳል ካለ
አረንጓዴ ቢጫው ፣ ቀዩም ካልጎደለ
ፍቅርን ካመጣ ፣ ቢሆንስ ምናለ
በማለት ለማስቆም ፣ ከቶም አልታገለ ።

ክርስቲያን እስላሙ ፣ መቼ ተለያይቶ
ይኖር ነበር እንጂ ፣ ተዋዶ ተጋብቶ
ለዘመናት በፍቅር ፣ የኖረ ነው ጸንቶ
ጠማማ አካሄዱን ፣ መች በክፋት አይቶ ።

አካሄዱን ሳያውቅ ፣ ሕዝቡ ሳይጠረጥር
ብዙም ሳይጓዙ ፣ ይፋ የሆነው ሚስጥር
ሁሉን የሚያዩበት ፣ ብልሹ መነጥር
ጸባቸው ከምነት ጋር ፣ ሆነ ያለጥርጥር ።

እምነት የለሹ ደርግ ፣ እርቆ ላይገፋ
ልቡ አብጦ ካለልክ ፣ ከንቱ ሲደነፋ
ቀይ ሽብር እያለ ፣ ግድያ ጭፍጨፋ
ግድያና እስራት ፣ ታውጆ በይፋ
የጁን ዋጋ አገኘ ፣ እሱም ተኖ ጠፋ ።

በሕዝብ የፈጸመው ፣ ያደረሰው በደል
ሞያ አሮ የያዘው ፣ ማሰርና መግደል
እሱም ተራው ደርሶ ፣ ጽዋውን ሲታደል
ውርደት ተከናንቦ ፣ ጠፋ ገባ ገደል ።

ደርግን ያሳዳደው ፣ ኢትዮጵያዊ አርበኛ
የት ነበር አይባል ፣ መጥቶ ድንገተኛ
በልቶ እማይጠረቃ ፣ በጠባብ ጎጠኛ
ሁሌም ለዘረፋ ፣ ሲያልም የማይተኛ
ድሉን ተዘረፈ ፣ በባንዶች ምንደኛ ።

ወንበዴው ወያኔ ፣ ድሉን ከህዝቡ ሰርቆ
ማንነቱን እንኳን ፣ የማያውቅ ጠንቅቆ
በዘር በሃይማኖት ፣ ጥላቻ ማነቆ
መስበኩን ጀመረ ፣ ግንጠላን ሰንቆ
አገርን ያፈርሳል ፣ ይሄው ባጭር ታጥቆ ።

እንዳንበሳ ገዳይ ፣ ሲፎክር ሲያቅራራ
ሃይማኖት አልባውን ፣ ደርጉን እየጠራ
ሰይጣናዊ እምነቱን ፣ ሲያስገባ በተራ
አንባሻ አስመስሎ ፣ አድርጎን ሸውራራ
የሰይጣኑን ምስል ፣ አረገው ባንዲራ ።

ምስክሩ ሰይጣን ፣ ዳኛውም ዲያቢሊስ
ደም የጠማው አውሬ ፣ ስራው የአርዮስ
ጫቱን አመንዥጊ ፣ ጋያውን የሚጎርስ
ከሌጊዮን ጋራ ፣ ማዕዱን የሚቆርስ ።

ከጥንት የወረስነው ፣ የቆመው ለላማ
የናት ሐገራችን ፣ የኢትዮጵያ እማማ
በደደቢት ደደብ ፣ ሰንደቁ ተግማማ
ተተክቷል ዛሬ ፣ በሰይጣኑ አርማ ።

ተንኮሉ ብዙ ነው ፣ የወያኔ ሴራ
ታሪኩ መች ያልቃል ፣ ቢተረክ ቢወራ
ብሄር በሄረሰብ ፣ እያለ የሚጣራ
አገር የሚያይበት ፣ አይኖቹ ሸውራራ
ካብ ኣይገባ ባንዳ ፣ አስመሳይ ኩታራ ።

ይብቃ ማጭበርበሩ ፣ የቁጩ ማስሩ
በሃሰት ወንጅሎ ፣ ባሰት መመስከሩ
ቅንድብን ተላጭቶ ፣ ህዝብን መመዝበሩ
በጠራራ ፀሀይ ፣ ካዝና መስበሩ ።

አርማቸው የሰይጣን ፣ አይበጅም ጨርሶ
ይሁን ለወያኔ ፣ ማሰሪያ ለበሶ ፣
አርማቸው የሰይጣን ፣ ስራቸው ይሁዳ
እንኳንስ ለወገን ፣ አይበጁ ለባዳ ፤

እምነት ያለው ወርዶ ፣ እምነት አልባው መጣ
ያሁኑ ይባስ ብሎ ፣ ፈጣሪ ሲቆጣ
ሉሲፈር አምላኪ ፣ ጭራሽ አይን ያወጣ
የሰይጣኑን ሰንደቅ ፣ ባገር ላይ አመጣ ።

የምናደርገውን ፣ ስራችንን እንወቅ
ቤልሆር ከፈጣሪ ፣ መቼም አይታረቅ
ከዕምነት ስፍራ ይውጣ ፣ የዲያቢሎስ ሰንደቅ
አስፈሪ ነውና ፣ የሚያመጣብን ጠንቅ ።

ባላምስት ማእዘን ፣ ኮከብ ምልክቱ
የሰይጣን አምልኮ ፣ መሆኑን ከጥንቱ
መመርመር ይበጃል ፣ ከስር መሰረቱ
ወያኔ እንደሆነ ፣ ታውቋል ክህደቱ
ተጠንቀቅ ወገኔ ፣ ከቶ እንዳትስቱ ።

ቀስ ብሎ ያመጣት ፣ በዘዴ አስታኮ
የወያኔ እምነት ፣ የሰይጣን አምልኮ
አትሳተፍ ሕዝቤ ፣ አትሁንለት ምርኮ
እሱው ይስገድለት ፣ ካሻው ተንበርክኮ ።

ከቤተ መቅደሱ ፣ ይሁን ከመስኪዱ
እንደየእምነታችሁ ፣ ላምላክ የምትሰግዱ
የአውሬውን አርማ ፣ ሰንደቁን አውርዱ
መቅሰፍት ሳያመጣ ፣ በጊዜ አስወግዱ ።

የቤተ ክህነት ፣ ዲያቆኑ ካህኑ
በሶስቱ ስላሴ ፣ በጌታ የምታምኑ
ፈጣሪያችሁንም ፣ እንዳታሳዝኑ
ወያኔን ትታችሁ ፣ በምነታችሁ ጽኑ
ጽላተ ሙሴውን ፣ በሱ እንዳትሸፍኑ ።

እንግዲህ ወገኔ ፣ እስላም ክርስቲያኑ
ባላማችሁ ጽኑ ፣ ለውጊያ ወስኑ
የሰይጣን አገልጋይ ፣ እኩይ ስለሆኑ
ስልጣን ሆነ እምነትን ፣ ስለማይመጥኑ
መንጥሮ ለመጣል ፣ አልሙ ወጥኑ ።

ስንቱን አየች አገር ፣ ስንት አስተናገደች
ሽቅብ እንደመውጣት ፣ ቁልቁል እየሄደች
ከሃይማኖት አልባው ፣ ሰይጣንጋ ደረሰች
ሶስት አይነት እምነቶች ፣ እያፈራረቀች
ያሁኑ ይባስ ሆነ ፣ ዛሬስ ተዋረደች ።

ባላገሩ

February 11, 2018


የወያኔ
ምልክት


የሰይጣን
ምልክት

**ለዋቢነት የሚከተሉትን ይመልከቱ።**

https://en.wikipedia.org/wiki/Church_of_Satan (Retrieved on 02/10/2018)
https://www.cnn.com/2015/12/11/living/5-things-satanists/index.html
(Retrieved on 02/10/2018)
http://www.dpjs.co.uk/symbols.html (Retrieved on 02/10/2018)